National ID
ብሔራዊ መታወቂያ

# የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 1284/2015 ላይ ለባለድርሻ አካላት የተዘጋጀ ስልጠና

መታወቅ ለመተማመን!

የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 1284/2015 ላይ ለባለድርሻ አካላት የተዘጋጀ ስልጠና

National ID
ብሔራዊ መታወቂያ

# ማውጫ

- የመታወቂያ ዓይነቶች እና የዲጂታል መታወቂያ ዓላማ እና መርሆዎች
- የዲጂታል መታወቂያ አስፈላጊነት እና አገልግሎት
- ለዲጂታል መታወቂያ የሚሰበሰቡ መረጃዎች እና አጠባበቅ ዓላማ እና መርሆዎች
- በህጉ የተካተቱ የወንጀል ኃላፊነትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ዓላማ እና መርሆዎች
- የመንግስት ተቋማት ኃላፊነት ዓላማ እና መርሆዎች

# የመታወቂያ ዓይነቶች

በየትኛውም ሀገር የሚገኝ የመታወቂያ ሥርዓት በሁለት የሚከፈል ሲሆን እነሱም

1. አገልግሎት ተኮር መታወቂያ (Functional ID) እና
2. መሰረታዊ መታወቂያ (Foundational ID) ናቸው፡፡

- አገልግሎት ተኮር የመታወቂያ (Functional ID) ማለት የተወሰነ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችል መታወቂያ ነው፡፡
- እንዲህ አይነት መታወቂያ፣ ከተሰጠበት አገልግሎት ውጭ ለሌሎች ነዋሪነትን እና ማንነትን በማረጋገጥ ለሚሰጡ አገልግሎቶች ተቀባይነት ላይኖራቸው ይችላል፡፡

# የመታወቂያ ዓይነቶች


## 2 መሰረታዊ መታወቂያ (Foundational ID)

- መሰረታዊ መታወቂያ (Foundational ID) ማለት በተሰጠበት ሀገር ውስጥ በየትኛውም ቦታ ተቀባይነት ያለው እና ማንነትን በማረጋገጥ ለሚሰጡ የትኛውም አገልግሎቶች ተቀባይነት ያለው የመታወቂያ አይነት ነው፡፡
  ከዚህም በተጨማሪ መሰረታዊ መታወቂያ (Foundational ID) ለአገልግሎት ተኮር መታወቂያዎች (Functional ID) እንደመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡

- መሰረታዊ መታወቂያ በተለያዩ ሀገራት የተለያዩ ስያሜዎች ሊኖሩት የሚችሉ ሲሆን ብሄራዊ መታወቂያ ወይም የዲጂታል መታወቂያ በብዛት መሰረታዊ መታወቂያ የሚጠራባቸው ስያሜዎች ናቸው፡፡

# ዓላማዎች

**በአዋጁ ላይ እንደተመለከተው የዲጂታል መታወቂያ ዓላማዎች**



ነዋሪዎች በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ሲንቀሳቀሱ በቀላሉ የመታወቅ መብታቸው እንዲረጋገጥ በማድረግ


ለሰብአዊ መብቶቸ አከባበር እና ለመልካም አስተዳደር መሻሻል አስተዋፅኦ ማድረግ፣

አገልግሎት  ማግኘት የሚፈልጉ ግለሰቦችን በቀላሉ  ለመለየት የሚያስችል የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በመዘርጋት በአገልግሎት ሰጪ እና አገልግሎት ተቀባይ መካከል እምነት እንዲጎለብት ማድረግ፣

ሕገ-ወጥ ተግባራትን መከላከል፣

# ዓላማዎች

## የቀጠለ..



ሀገር አቀፍ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት በማደራጀት ሀገራዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና እቅዶች ሲቀረጹ እና የልማት ሥራዎች ሲከናወኑ ድግግሞሽን መቅረፍ፣ በዚህም የሀብት ብክነትን መቀነስ እና አካታችነትን ማጎልበት፤

የነዋሪዎችን የዲሞግራፊክ እና ባዮሜትሪክ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት፣ ለሌሎች መንግስታዊ እና መንግስታዊ ላልሆኑ አካላት የመታወቂያ ሥርዓት መረጃ ምንጭ ሆኖ ማገልገል፣

አገልግሎት ተኮር የሆኑ የመታወቂያ ሥርዓቶች ወደ ዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት እንዲሸጋገሩ ማጠናከር።

# መርሆዎች

1. አካታችነት
2. አስተማማኝነት
3. የተመጠነ መረጃ
4. ተናባቢነት

# የዲጂታል መታወቂያ አስፈላጊነት

- የመታወቅ መብትን ለማረጋገጥ
- በልማት እቅድና ፕሮግራሞች ዘርፍ
- በፋይናንስ ዘርፍ
- በፍትህ ዘርፍ
- በትራንስፖርት ዘርፍ
- በግብርናው ዘርፍ
- በጤናው ዘርፍ



# በፍትህ ዘርፍ

- ወንጀልን ለመከላከል
- ወንጀል ከተፈፀመ በሀላ አጥፊዎችን ለመለየት
- ሀሰተኛ ምስክርነትን ለመከላከል እና ሀቀኛ ምስክሮችን ለመለየት
- የወንጀል ደጋጋሚዎችን ለመለየት
- የማረምና ማነፅ እንዲሁም መልሶ መቀላቀል ስራን ለማዘመን





# በፋይናንስ ዘርፍ

- የባንክ እና የፋይናንስ ዘርፍ ከመጭበርበር ለመታደግ
- የገጠር ፋይናንስ ሥርዓቱን በማዘመን

  ከህገ ወጥ ተግባራት ለመታደግ
- **ለምሳሌ፡ የተበዳሪዎችን ማንነት በቀላሉ ለመለየት፣**

  የተለያዩ የክፍያ እና ገንዘብ መቀበያ ስርዓቶችን ጋር
- ለማቀናጀት
- የገቢ ስርዓቱን ለማዘመንና ለማቀላጠፍ

  የንግድ ፈቃድ ተመዝጋቢዎችን ማንነት በቀላሉ ለመለየት

# ከሃገራዊ ደህንነት ዘርፍ

- ሀገራዊና የነዋሪዎችን ሁለንተናዊ ደህንነት ለማረጋገጥ
- የድንበር ሽግግር ቁጥጥር ማገዝ
- በህግ ለተፈቀዱ የደህንነት ስራዎች የመረጃ ምንጭ

# የትራንስፖርት ዘርፍ

- የመንጃ ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓቱን ለማዘመን
- ስማርት ትራንስፖርት ለመተግበር





## በግብርናው ዘርፍ

- ከማዳበሪያና ከምርጥ ዘር  ስርጭት ፍትሃዊነት
- የሴፍትኔት ተጠቃሚዎች ውጤታማነት

## በሲቪል ሰርቪስ ዘርፍ

- የሲቪል ሰርቫንቱን ቁጥር በትክክል ለማወቅ
- ትክክለኛ የትምህርት ማስረጃ ያላቸውን ከአጭበርባሪዎች ለመለየት
- የሲቪል ሰርቫንቱ አገልግሎቶችን በቀላሉ ለመስጠት ለምሳሌ የመጓጓዣ
- ህገወጥ ደሞዝና ክፍያዎችን ለማስቀረት

## በከተማ ልማት ዘርፍ

- የኮንደሚኒምና ሌሎች የቤት መርሀግብር ተጠቃሚዎችን
- አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ለመለየት እና ትክክለኛ እቅድ ለማቀድ

## በጤናው ዘርፍ

- የጤና ኢንሹራንስ ተጠቃሚዎችን ፍትሃዊነት ለመዘርጋት
- የጤናውን ዘርፍ በቴክኖሎጂ ለማዘመን
- ትክክለኛ የጤና እቅድ ለማቀድና ለመፈጸም

## በትምህርት ዘርፍ

- የጤና ኢንሹራንስ ተጠቃሚዎችን ፍትሃዊነት ለመዘርጋት
- የጤናውን ዘርፍ በቴክኖሎጂ ለማዘመን
- ትክክለኛ የጤና እቅድ ለማቀድና ለመፈጸም



# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

- የዲጂታል ክፍያዎችንና የኤሌክትሮኒክስ ግብይት
- የሳይበር ደህንነት ጥበቃ ለማጠናከር፣
- የቴሌኮም አገልግሎትን ለማዘመን፣
- ተንቀሳቃሽ የገንዘብ ዝውውርን (mobile money) ለማዘመን

# ሥራና ክህሎት

- አላግባብ የስራ እድል ተጠቃሚነትን ለመከላከል፣
- ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ የስራ ፈጠራን (Entrepreneurship) ለማጎልበት፣
- በቴክኖሎጂ የተደገፈ የስራ ፈጠራን (technology start-up) ለማበረታታት፣

# የዲጂታል መታወቂያ አገልግሎት

- በኢትዮጵያ በአሁኑ ሰአት ተግባራዊ ለማድረግ በሙከራ ላይ የሚገኘው የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት (Foundational ID) መሰረታዊ መታወቂያ የሚሰጥበት ስርዓት ነው፡፡
- የዲጂታል መታወቂ ማለት ማንኛውም በሀገሪቱ ውስጥ የሚኖር ሰው ተቋሙ ወይም በተቋሙ ውክልና የተሰጠው አካል በሚያደርገው የምዝገባ ሂደት የባዮሜትሪክ እና ዲሞግራፊክ መረጃዎችን በመስጠት ከተመዘገበ በኋላ ማንነቱን ለማረጋገጥ የሚሰጥ ልዩ ቁጥር(Unique Number) ነው፡፡
- **ይህ ልዩ ቁጥር ወይም ዲጂታል መታወቂ የሚመነጨው ከግለሰቡ የባዮሜትሪክ እና ዲሞግራፊክ ዳታ በመሆኑ፣ ግለሰብን በልዩ ሁኔታ ለመለየት የሚስያስችል አስተማማኝ የመታወቂ ስርዓት ነው፡፡**

# የዲጂታል መታወቂያ አገልግሎት...


- በአዋጁ ላይ በግልፅ እንደተመለከተው የዲጂታል መታወቂያ የአንድን ነዋሪ ማንነትን ለማስረዳት ወይም ለማረጋገጥ እንደ ህጋዊ እና በቂ ማስረጃ ተደርጎ እንደሚወሰድ እና ማንኛውም ተጠቃሚ አካል ለነዋሪው ለሚሰጠው አገልግሎት የዲጂታል መታወቂያ እንደ አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ የሚያደርግ አሠራር በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ፍቃድ መዘርጋት እንዳለበት ተደንግጓል፡፡
- ስለሆነም አሁን በኢትዮጵያ ተግባራዊ የሚደረገው ዲጂታል መታወቂያ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ተቀባይነት ያለው እና ማንነትን በማረጋገጥ ለሚሰጡ አገልግሎቶች እንደ አስገዳጅ የመታወቂያ አይነት የሚወሰድ ሲሆን፣ በዚህ መታወቂያ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም ሰው በወንጀል እንደሚጠየቅ አዋጁ በሚከተለው መልኩ ደንግጓል፡፡

# የዲጂታል መታወቂያ አገልግሎት...


- በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትለው በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች መሠረት ስልጣን ባለው አካል የተሰጠን ዲጂታል መታወቂያን እንደ ህጋዊ መታወቂያ ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም ማንነትን ብቻ በማረጋገጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በዲጂታል መታወቂያ ለመስጠት ፍቃደኛ ያልሆነ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀፅ 19 ላይ የተመለከተውን የመተባበር ግዴታ የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከአስር ሺህ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል"
- ከላይ እንደተገለጸው ዲጂታል መታወቂያ የሚባለው ልዩ ቁጥሩ ሲሆን፣ ይህንን መታወቂያ በካርድ መልኩ መያዝ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ተገቢውም ክፍያ በመፈፀም ከተቋሙ ወይም ተቋሙ ውክልና ከሰጠው ማንኛውም አታሚ ድርጅት የመታወቂያ ካርዱን ማግኘት የሚቻልበት ስርዓት ተዘርግቷል።

# ለዲጂታል መታወቂያ የሚሰበሰቡ መረጃዎች

- በአዋጁ ላይ በግልፅ እንደተመለከተው ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ሰው



Eye scan



Finger scan



Picture

1 የባዮሜትሪክ መረጃ



Demographic Data



Consent form

2 ዲሞግራፊክ መረጃ

- በመስጠትና በመመዝገብ የዲጂታል መታወቂያ የማግኘት መብት አለው።

ነዋሪው የዲጂታል መታወቂያ ለመውሰድ እሱነቱን ለማረጋገጥ የሚያገለግሉ የመታወቂያ ሰነዶች እና ሌሎች በተቋሙ ተቀባይነት ያላቸውን ሰነዶች ወይም የሰው ምስክር ማስረጃዎችን በመጠቀም በማረጋገጥ መመዝገብ ይኖርበታል ይችላል።

# ለዲጂታል መታወቂያ የሚሰበሰቡ መረጃዎች

- ከላይ እንደተመለከተው ወደ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የሚገባ የግል መረጃ የእያንዳንዱን ተመዝጋቢ የዲሞግራፊክ መረጃ እና ባዮሜትሪክ መረጃን ያካተተ መሆን ያለበት ሲሆን፣ የዲሞግራፊክ መረጃ የሚባሉትም ስም ፣ የአባት ስም ፣ የአያት ስም ፣ ወይም በዚህ መልክ የተደራጀ ህጋዊ ስም ለሌለው ተመዝጋቢ ተቋሙ ህጋዊ የሆነውን ስያሜ ወይም ተመዝጋቢው በአካባቢው ማህበረሰብ የሚጠራበትን ስም፣ ዜግነት፣ የትውልድ ቀን፣ ወር እና ዓመት፣ ፆታ፣ መኖሪያ አድራሻ ሲሆኑ እንደአስፈላጊነቱ ስልክ ቁጥር፣ የኢሜይል አድራሻ እና ፖስታ አድራሻንም ሊያካትት ይችላል፡፡

# ለዲጂታል መታወቂያ የሚሰበሰቡ መረጃዎች

- የሚሰበሰቡት የባዮሜትሪክ መረጃዎች ደግሞ የአስር ጣት አሻራ፣ የሁለቱም አይኖች ብሌን እና የፊት ገፅታ ናቸው፡፡
- እነዚህን የባዮሜትሪክ እና ዲሞግራፊክ መረጃዎች የሰጠ ማንኛውም ሰው የዲጂታል መታወቂያ ማግኘት ይችላል፡፡
- አንዳንድ ጊዜ የባዮሜትሪክ መረጃዎችን ለመስጠት የሚቸገሩ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡
- ለምሳሌ ጣት የሌለው ሰው፣ በእርጅና እና በተለያዩ ምክንያቶች አሻራቸው የማይነበብ ሰዎች በሚኖሩበት ጊዜ እና መሰል ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ፣ በዲሞግራፊክ መረጃ ብቻ መታወቂያውን መስጠት የሚገባ ስለመሆኑ በአዋጁ ተደንግጓል፡፡

# የመረጃ አጠባበቅ ስርዓት

- የዲጂታል መታወቂያ ለማግኘት የሚሰበሰቡ መረጃዎች በተለይም የባዮሜትሪክ መረጃዎች በጥንቃቄ ካልተያዙ ለተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ሊያጋልጡ ይችላሉ፡

- ስለዚህ ለዲጂታል መታወቂያ የተሰበሰቡ መረጃዎች በጥንቃቄ መያዝ ያለባቸው በመሆኑ አዋጁ ተቋሙ የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት የግል መረጃን በአስተማማኝነት የሚይዝ ጠንካራ የመረጃ አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት አለበት፤ በሚል የደነገገ ሲሆን፡

# የመረጃ አጠባበቅ ስርዓት

- አሰራርና ህግን ጠብቆ በዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ለተሰበሰበ የማንኛውም ተመዝጋቢ ግላዊ መረጃ ያለ ተመዝጋቢው ፈቃድ ለሌላ ሰው መግለጽ፣ ማስተላለፍም ሆነ እንዲለወጥ መፍቀድ የተከለከለ መሆኑን ህጉ በግልፅ አስቀምጧል፡፡
- ይህን ክልከላ መተላለፍም በወንጀል የሚስጠይቅ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 25 ላይ ተደንግጓል፡፡
- ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ለፍትህ ስራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በህግ ስልጣን ለተሰጠው ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት የግል መረጃው ለሚመለከተው ህጋዊ አካል ሊገለጽ ወይም ሊተላለፍ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡



# የወንጀል ተጠያቂነት

- በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትለው በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች መሠረት ስልጣን ባለው አካል የተሰጠን ዲጂታል መታወቂያን እንደ ህጋዊ መታወቂያ ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም ማንነትን ብቻ በማረጋገጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በዲጂታል መታወቂያ ለመስጠት ፍቃደኛ ያልሆነ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀፅ 20 ላይ የተመለከተውን የመተባበር ግዴታ የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከአስር ሺህ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

- በዚህ አዋጅ አንቀፅ 16(3)፣ (4) ወይም (5) ስር የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከአስር ሺህ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤



# የወንጀል ተጠያቂነት

- በዚህ አዋጅ አንቀፅ 16(9) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ዲጂታል መታወቂያ ለማግኘት የተሰበሰቡ መረጃዎችን ሆነ ብሎ ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ ማንኛውም ሰው ከአንድ አመት እስከ አምስት አመት ወይም እንደነገሩ ክብደት እስከ ስምንት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፤

- በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) ላይ የተመለከቱት ጥፋቶች የተፈጸሙት የሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ከሆነ ከአንድ መቶ ሺህ ብር እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።



# የወንጀል ተጠያቂነት

- በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) ላይ የተመለከተው ጥፋት የተፈጸመው የሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ከሆነ ከሶስት መቶ ሺህ ብር እስከ ስምንት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣

- በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) ስር የተመለከተው ድርጊት የተፈጸመው በቸልተኝነት ከሆነ ቅጣቱ ከስድስት ወር እስከ አንድ አመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከአስር ሺህ ብር እስከ ሰባ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይሆናል፣



# የተቋማት ኀላፊነት

- የሕጉን መውጣትና የመታወቂያውን አስፈላጊነት ለሰራተኞች መረጃውን ማውረድ፣
- ከስራችን ጋር በማስተሳሰር ተግባራዊ ማድረግ{ ሰነዶች፣ የፋይናንስ ተቃማት---}
- መታወቂያውን እንደ አንድ ህጋዊ መታወቂያ መገልገል፣
- አዋጁ ሲጣስ  የህግ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ{ፖሊስ፣ አቃቤ ህግ}፣
- ከተቃማችን ጋር ትብብር ማድረግ
- በአጠቃላይ ለዲጂታል መታወቂያ አተገባበር አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ

National ID
ብሔራዊ መታወቂያ

# Thank You